Amharic | አማርኛ

MULTICULTURAL CENTRE FOR WOMEN'S HEALTH

# የሴቶች ግርዛት በአውስትራሊያ

የሴት ግርዛት አንዳንድ ጊዜ የሴት ብልት መቁረጥ ወይም የሴት ብልት ግርዛት/መቁረጥ (FGM/C) ተብሎ ይጠራል። ለህክምና ባልሆኑ ምክንያቶች የሴት ብልት አካባቢን መቁረጥ ወይም ጉዳት ማድረስን ያካትታል። የሴቶች ግርዛት፣ ለሴቶች እና ልጃገረዶች ምንም አይነት የጤና ጠቀሜታ የለውም፤ ሆኖም በጾታዊ እና በስነ ተዋልዶ ጤንነታቸው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል።

በቤተሰብ እና በማህበረሰብ አባላት እንደ አስፈላጊ የባህል ልምድ ሊቆጠር የሚችል ጎጂ ተግባር ነው። ነገር ግን፣ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ልምዶችን ትተን ባህላችንን የምናከብርበት እና ለባህላችን ዋጋ የምንሰጥባቸው መንገዶች አሉ።

የራሳችንን አካል ለመቆጣጠር እና ለመጠበቅ ሁላችንም በክብር እና በአክብሮት መታከም አለብን። ይህ የሁሉም ሰው መብት ነው። በሁሉም ስቴቶች እና ግዛቶት ላይ የሴቶች ግርዛት ድጋፍ፣ ምክር እና መረጃ አለ።

***ሰብአዊ መብቶች***

*የሴቶች ግርዛት በአለም አቀፍ ደረጃ የልጃገረዶች እና የሴቶች ሰብአዊ መብት መጣስ ተደርጎ ይወሰዳል።*

*ይህ ግብአት፣ በአውስትራሊያ መንግስት የገንዘብ ድጋፍ በተደረገው የግርዛት/FGM/C ስልጠና (SWIFT) ፕሮጀክት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ተዘጋጅቷል። መጨረሻ የተሻሻለው፦ መጋቢት 2026*

**እነዚህ በመላው አውስትራሊያ ላሉ ሴቶች፣ ልጃገረዶች እና ቤተሰቦች አገልግሎት እንዴት እንደሚያገኙ እና እንደሚጠቀሙ መረጃ፣ ምክር እና እገዛ የሚሰጡ የድጋፍ አገልግሎቶች ናቸው።**

**South Australia - The Refugee Health Service**
**(ሳውዝ አውስትራሊያ - የስደተኞች ጤና አገልግሎት)**
ስልክ ቁ፦ 08 7133 996
ድህረ ገጽ፦ www.calhn.sa.gov.au/refugee-health-service

**Queensland - True Relationships and Reproductive Health**
**(ኩዊንስላንድ - እውነተኛ ግንኙነቶች እና የስነ ተዋልዶ ጤና)**
ስልክ ቁ፦ (07) 3250 0240
ኢመይል፦ culturallyresponsive@true.org.au

**New South Wales - NSW Education Program on Female Genital Mutilation/Cutting (FGM/C) (ኒው ሳውዝ ዌልስ - የ ኒው ሳውዝ ዌልስ የትምህርት ፕሮግራም በሴት ብልት ግርዛት/መቁረጥ)**
ስልክ ቁ፦ (02) 9840 4182 ወይም (02) 9840 3877
ድህረ ገጽ፦ www.betterhealth.vic.gov.au/health/conditionsandtreatments/female-genital-cutting-circumcision-fgc
ኢመይል፦ WSLHD-FGMEducationProgram@health.nsw.gov.au

**Western Australia - Womens Health Strategy and Programs**
**(ዌስተርን አውስትራሊያ - የሴቶች ጤና ስትራቴጂ እና ፕሮግራሞች)**
ስልክ ቁ፦ 08 6458 1152
ኢመይል፦ KEMH.WomensHealthStrategyandPrograms@health.wa.gov.au

**Victoria - The Family and Reproductive Rights Program**
**(ቪክቶሪያ፤ የቤተሰብ እና የስነ ተዋልዶ መብቶች ፕሮግራም)**
ድህረ ገጽ፦ www.betterhealth.vic.gov.au/health/conditionsandtreatments/female-genital-cutting-circumcision-fgc
ስልክ ቁ፦ በአከባቢዎ ያለውን ድርጅት ለማነጋገር ከላይ ያለውን ድህረ ገጽ ይጎብኙ
*የሴት ብልት ቀዶ ጥገና (deinfibulation) አገልግሎቶችን ለማግኘት Royal Women Hospital FGM clinic (የሮያል ዉሜን ሆስፒታል የግርዛት እና የሴት ብልት መቁረጥ ክሊኒክን) ያነጋግሩ።*

**Tasmania - Redcross, Bicultural Community Health Program**
**(የታዝማኒያ ቀይ መስቀል ፣ የባይካልቸራል ማህበረሰብ የጤና ፕሮግራም)**
ስልክ ቁ፦ (03) 6235 6077
ድህረ ገጽ፦ www.redcross.org.au/migration/bicultural-health-service-in-tasmania
ኢመይል፦ Tasbiculturalhealth@redcross.org.au

ከእንግሊዘኛ ውጭ በሌላ ቋንቋ ሰው ማነጋገር ከፈለጉ **ለብሔራዊ የትርጉም እና አስተርጓሚ አገልግሎት** (TIS National) በ **131 450** ይደውሉ። **ነፃ እና ሚስጥራዊ አስተርጓሚ** ከላይ ከተዘረዘሩት ከማንኛውም ስልክ ቁጥር ጋር ሊያገናኝዎት ይችላል።

## የጤና ጉዳዮች

የሴቶች ግርዛት፣ የአጭር እና የረዥም ጊዜ የጤና መዘዞች ያሉት ሲሆን፣ የሚከተሉትን ይጨምራል፦

- የአካል ጤና ጉዳዮች፦ ከባድ ህመም፣ ደም መፍሰስ፣ ኢንፌክሽን ፣ ጠባሳ፣ የወር አበባ እና የሽንት ችግሮች (ለምሳሌ ሲሸኑ)።
- የእርግዝና እና የወሊድ ስጋቶች፦ ረዘም ላለ ጊዜ ምጥ ማማጥ፣ መቀደድ እና ደም መፍሰስ።
- የስነ-ልቦና ተጽእኖዎች፦ የስሜት ቀውስ፣ ጭንቀት እና የወሲብ ደስታ መቀነስ፣ ወይም በግንኙነት ውስጥ ችግሮች መኖር።

አንዳንድ ሴቶች እና ልጃገረዶች ምንም ምልክት ላያሳዩ ይችላሉ፣ ሌሎች ደግሞ ብዙ ችግሮች ሊያጋጥማቸው ይችላል። ማንኛቸውም ስጋቶች ወይም ችግሮች እያጋጠሙዎት ከሆነ፣ ድጋፍ ለማግኘት የጤና እንክብካቤ አቅራቢን ያነጋግሩ።

## የሴት ግርዛት የት ነው የሚተገበረው?

በዓለም ዙሪያ ከ 230 ሚሊዮን በላይ ሴቶች እና ልጃገረዶች ተገርዘዋል። ልምዱ በአፍሪካ፣ በመካከለኛው ምስራቅ እና በእስያ ባሉ ማህበረሰቦች እና የተወሰኑ ብሄረሰቦች ውስጥ ሊገኝ ይችላል።

***በአውስትራሊያ ውስጥ የሚኖሩ ወደ 53,000 የሚገመቱ ሴቶች እና ልጃገረዶች ግርዛት/FGM/C አድርገዋል።[1]***

የሴቶች ግርዛት በሚደረጉባቸው አገሮች ውስጥ ያሉ ሁሉም ማህበረሰቦች ግርዛትን አያደርጉም፣ አንዳንድ ጊዜ የሚተገበረው በትንሽ አናሳ ማህበረሰቦች ብቻ ነው።

የሴቶች ግርዛት አመጣጥ አይታወቅም፣ እንዲሁም ሃይማኖታዊ ጠቀሜታም የለውም። በዓለም ዙሪያ ያሉ ሀገራት ከዚህ ጎጂ ድርጊት እየራቁ እንዲሁም ህገወጥ እያደረጉት ነው።

*1 የአውስትራሊያ የጤና እና ደህንነት ተቋም (Australian Institute of Health and Welfare)። (2019)። በአውስትራሊያ ውስጥ የሴት ብልት ግርዛት/መቁረጥ ስርጭትን ለመገመት (Cat. no. PHE 230)። Canberra: AIHW (ካንቤራ፦ አውስትራሊያ የጤና እና ደህንነት ተቋም AIHW)*

## የተለያዩ ዓይነት የሴቶች ግርዛቶች አሉ።

የሴቶች ግርዛት ሁልጊዜ አንድ አይነት አይደለም፤ ስለሆነም በሴት ብልት አካባቢ ላይ የተለያዩ ለውጦችን ሊያስከትል ይችላል። የግርዛት አይነት በማህበረሰቦች እና በብሔረሰቦች መካከል ሊለያይ ይችላል። አንዳንድ ዓይነቶች ትናንሽ ለውጦችን ብቻ ያካትታሉ፣ ሌሎች ደግሞ የበለጠ ዋና ዋና ሂደቶችን እና የተወሳሰቡ እክሎችን ያካትታሉ።

አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ሴቶች በጣም ሰፊ የሆነ ግርዛት ተደርጎባቸዋል፤ ይህም የሴት ብልት መክፈቻ ማጥበብን ያካትታል።

እንደዚህ ዓይነት ግርዛት የተገረዙ ሴቶች፣ በእርግዝና እና በወሊድ ወቅት የሐኪም ወይም አዋላጅ ድጋፍ ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

### በአውስትራሊያ ውስጥ ስለ ሴት ግርዛት ህጉ ምን ይላል?

***ግርዛት ከህግ ጋር የሚጻረር መሆኑን ማወቅ አስፈላጊ ሲሆን፣ እምቢ የማለት መብትም አለዎት።***

የሚከተሉት ማድረግ ከህግ ጋር የሚጻረር ነው፦
- *የሴት ብልት ማንኛውንም ክፍል ማስወገድ ወይም መቁረጥ*
- *የሴትን ብልት አካባቢ መስፋት ወይም እንደገና መስፋት*
- *የሴት ብልት መክፈቻ ማጥበብ*
- *ቂንጥርን መቁረጡ ወይም መብሳት*
- *በሴት ብልት አካባቢ ላይ ጉዳት ማድረስ ወይም ማቁሰል*

ህጉ አንድ ሰው የሚከተሉትን እንዳያደርግ ይከለክላል፦
- *ሴት ወይም ሴት ልጅ መቁረጥ*
- *አንድን  ሰው እንዲቆረጥ ከአውስትራሊያ ውጪ መውሰድ*
- *አንድን ሰው እንዲቆረጥ ከአውስትራሊያ እንዲወጣ መርዳት*

የሚከተሉትን ማድረግ የለብዎትም፦
- *የግርዛት ስርአት ማካሄድ*
- *የስርአቱን  ሂደት ለማከናወን ማገዝ*
- *የስርአቱን  ሂደት የሚያከናውን ሰው መፈለግ*

***የሴቶች ግርዛት እስከ 21 ዓመት እስራት ያስቀጣል።***

አንዳንድ ቤተሰቦች ወደ ትውልድ አገራቸው ሲመለሱ የሴቶች ግርዛትን እንዲቀጥሉ ጫና ሊሰማቸው ይችላል። እምቢ የማለት መብት እንዳለዎት ማወቅ አስፈላጊ ነው። በአውስትራሊያ እና በአለም ዙሪያ ያሉ ብዙ ቤተሰቦች ይህንን አሰራር ላለመቀጠል ይመርጣሉ፤ እናም ሴት ልጅዎን ከጉዳት መጠበቅ ሙሉ በሙሉ ምንም ችግር የለውም።